ግሬስ ፌሎሽፕ ኢንተርናሽናል

## በመስቀሉ ለሚገኝ ነጻነት የቀረበ መመሪያ

ይህን በምታነብበት ጊዜ በትልቅ ቀውስ ውስጥ ልትሆን ትችላለህ፡፡ ሰው ከድቶህ እግዚአብሔርም በፋንታው ይረዳህ ዘንድ ፈጽሞ የራቀብህም መስሎህ ይሆናል፡፡ የሚያስፈልጉህ ነገሮች ሊሟሉልህ ባልቻሉበት መልኩ የተወደድህ ሳይመስልህ አድገህ ሊሆን ይችላል አልፎም ራስህን ተቀብለህም ሆነ ወድደኸው አታውቅም ይሆናል፡፡

አንድ ሰው ህይወትን ለመቋቋም በሚያደርገው ትግል የሚሰማው የመሸነፍና ብቁ ያለመሆን ስሜት ከመካከለኛ የመጫጫን(ድብርት) ስሜት አንስቶ ራስን ለማጥፋት እስከማሰብ ያደርሰዋል፡፡ ከእንዲህ አይነቱ ስሜት የተነሳ ከምትወዳቸው ጋር ያለህ ግንኙነት እየሻከረብህ መጥቶ ለመፍረስ አፋፍ ላይ ደርሶ ሊሆን ይችላል ወይንም ሊስተካከል እንደማይችል ሆኖ ተበላሽቶብህም ይሆናል እነዲህ ባለ ሁኔታ ውስጥ ተሰፋህ መንምኖ አልያም ተሰፋ መቁረጥ ውጦህ ከሆነ ይህ መልእክት አንተ ላለህበት ሁኔታ የተዘጋጀ ነው፡፡

እግዜአብሔር ልጁን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በመስቀል ላይ ለአንተ ኃጢያት እንዲሞት፣ ከሞትም አስነስቶ በእርሱ በኩል ድል ላለበት የተትረፈረፈ ህይወት የሚያስፈልጉትን ነገሮች ሁሉ ሊሰጥህ እርሱን እስኪልክ ድረስ አንተን ወዶሃል፡፡ የእርሱ መስዋእትነት እግዚአብሔር የአንተን ሐጢአት ይቅር እንዲል የሚያስችለው መሆኑን ዛሬ ታምን አልያም አታምንም ይሆናል፡፡ የማታምን ከሆነ ይህ ግልጽ መልእክትና መልእክቱንም ለማሳየት የቀረቡት ሥዕላዊ መግለጫዎች የእርሱን ማለትም የክርስቶስን ህይወት እንድትቀበል በማድረግ ህይወትህን ሊለውጡ የሚችሉ ናቸው፡፡

ምናልባትም ክርስቶስን አምነህ ነገር ግን በክርስተና ህይወትህ በትግል ላይ ያለህ ወይም ድል መንሳት ተስኖህ በሽንፈት የምትመላለስና ከዚህ ህይወት መውጫውን የምትፈልግ ትሆናለህ ከእነዚህ ውስጥ አንዳቸው የአንተን ሁኔታ የሚገልጽ ከሆነ እግዚአብሔር እውነቱን እንዲገልጥልህ በጸሎት መንፈስ መጽሀፍ ቅዱስህን ከፍተህ የሚከተሉትን ሀሳቦች አጥናቸው፡፡

### የተፈጠርክበት ንድፍ

ክቡ ሥዕል የሚያመለክተው ሰው መንፈስ፣ ነፍስ እና አካልን አካቶ እንደያዘ እንደ ባለ ሶስት ክፍል ፍጡር መሆኑን ነው (1 ተሰ 5፡23)፡፡ አካላችን በዙሪያችን ካሉት ነገሮች ጋር በስሜት ህዋሳቶቻችን አማካኝነት መገናኘት እንድንችል ያደርገናል። ነፍስ ወይም ስብዕና የአእምሮን፣ የፈቃድ እና የስሜት ተግባራትን ያካተተ ነው አንዳችን ከሌላችን ጋር እንድንግባባም ያስችለናል፡፡ መንፈሳችን ደግሞ ዳግም በመወለድ በመነፈስ ቅድስ ህያው በሚሆንበት እና የመንፈሱ ማደሪያ በሚሆንበት ጊዜ ችሎታችንን ገደቦቻችንን እና ሁኔታዎቻችንን አልፈን እንድንሻገራቸው ያስችለናል፡፡

## የክቡ ስዕል ማብራሪያ




መንፈሳችን ወይ ከአዳም- የሰይጣን ቤተሰብ (ከታች ያለውን የመስመር ሥዕል ይመልከቱ) አልያም ደግሞ ከክርስቶስ - የእግዚአብሔር ቤተሰብ ጋር የተዛመደ ሊሆን ይችላል፡፡ እኛ ወደ አለም ተወልደን የመጣነው የአዳም ዘር ሆነንና የእርሱን ተፈጥሮ ተካፋዮች ሆነን ነው፡፡ ያ ማለት ደግሞ መንፈሳችን ለእግዚአብሔር የሞተና ለሰጣን ደግሞ ሕያው የሆነ ነው ማለት ነው፡፡ እኛ በተሳሳተው ቤተሰብ ውስጥ ነን! ህይወታችን ከመጀመሪያው አባታችን ከአዳም የመጣ እንደመሆኑ እና የዝርያችንም ሰንሰለት ከእርሱ የተቆራኘ እስከሆነ ድረስ እርሱ ኃጢአትን ባደረገ ጊዜ በእርሱ ውስጥ ሆን እኛም አድርገናል፡፡ ስለዚህም እኛ በአካል ከመወለዳችን በፊት ሐጢአተኞች ሆነናል፡፡ ይህ ተፈጥሮአችን ደግሞ ኃጢአትን እንድናደርግ ምክንያታችን ሆንዋል (ሮሜ 3፡23) ፡፡ ምንም እንኳ በሰው እይታ መልካም የሆነውን ሕይወት እየኖርን ቢሆንም እንኳ በመንፈሳዊው ዳጋመኛ ልደት ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብ እስካልተቀላቀልን ወይም

እስከንቀላቀል ድረስ ከእርሱ ተለይተናል። በሥዕሉ ላይ እንደሚታየው ከአዳም ባገኘነው ህወት የሚቀጥል ሁሉ ፍጻሚው የሚሆነው በሲኦል ነው (ሮሜ 6፡23) ፡፡

**የሚያስፈልግህ**

በክቡ ሥዕል ውስጥ ያለው "ደንነት"(1) የሚለው ቃል መንፈሳዊ ልደት ሊኖረን ይገባል ማለት ነው፡፡ ልክ በባለ መስመሩ ሥዕል ላይ እንዳየነው የአዳምን ህይወት ለቀን ልንወጣ እና የዘላለም ህይወት ወደ ሆነው ወደ ክርስቶስ ህይወት ልንወለድ የምንችለው በዚህ መንገድ ብቻ ነው (ዮሐ 3፡3) ፡፡ በመንፈስ ለመወለድ በተሳሳተ ህይወት ውስጥ እንዳለን እና ከዚያም የተነሳ ኃጢአተኞች ሆነን ልናስወግደው ከማንችለው የኃጢአት ውጤት ጋር እንደተወለድን ማወቅና እንዲሁም መናዘዝ ይኖርብናል፡፡ ከዚያ ለኃጢያችን ሞቶልናልና ክርስቶስን ወደ ህይወታችን መቀበል አለብን፡፡

በመንፈስ በመወለድ ውስጥ የክርስቶስን የመንፈስ ህይወት በእምነት ሆነው በመንፈሳቸው የሚቀበሉት ከእርሱ ጋር አንድ መንፈስ ይሆናሉ (1 ቆሮ 6፡17) ፡፡ በፈተና ላይ ድል እንዲኖራቸው እና የክርስቶስን ህይወት በህይወታቸው እንዲለማመዱት የደንነታቸው ማረጋገጫ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ "ማረጋገጫ" (2) መሰረት ሊያደርገው የሚገባው በእግዚአብሔር የማይቀለበስ ቃል እውነታዎች ላይ መሆን አለበት አልያ ግን አንድ ጊዜ ብቻ ብልጭ ብሎ የሚጠፋ ይሆናል፡፡

ለመዳን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በግል እንዳመኑ የሚያውቁ (በአእምሯቸው) ብዙዎች አሁንም ድረስ እውነተኛ ማረጋገጫ ጎድሏቸዋል ምክንያቱም በመዳናቸው እርግጠኞች አይደሉምና ነው፡፡ ምንም እንኳ ተጨባጭ የምንላቸው እውነታዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተብራሩ ወይም በቁሳዊው አለም የሚገኙ ቢሆኑም በልጅነት ጊዜ ከነበረ መገፋት የተነሳ በሚፈጠሩ የስሜት ጉዳቶች ወይም ግጭቶች ምክንያት የሰው ስሜት ( ወይም ስሜታዊ ህዋሶች) ከተጨባጭ እውነታዎች ጋር እምብዛም አይዋሀዱም፡፡ ስለዚህም ብዙዎቹን ነገሮች እንዳሉበት ሁኔታ ሳይሆን በተለየ መንገድ ነው የምናያቸው ፡፡ ኢየሱስ ወደ ውስጣችን ገብቶ እነኝህን ጉዳቶች ካልፈወሰ እና ስሜታችንን ካላስተካከለ በስተቀር እውነታዎችን አንዳሉ መቀበል የሚከብደን ይሆናል ፡፡

የቆየም ይሁን አዲስ አማኝ ሁሉ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር አስተማማኝ እና ዘላለማዊ ወደ ሆነ መንፈሳዊ ግንኙነት ገብቷል ( ዮሐ 5፡24 ) ፡፡ ደግሞም በዚያ "መተማመኛ"(3) ላይ ሊደገፍና ሊተማመንበትም ይገባዋል፡፡ ምንም እንኳን ብዙዎቹ አማኞች ክርስቶስን እንደተቀበሉ ቢያውቁም ጥቂቶቹ ብቻ ግን በእርሱ ተቀባይነት እንዳላቸው የተረዱ እና ያንንም እውነታ የሚለማመዱ ሆነው እናያለን፡፡ ብዙዎች በክርስቶስ ባገኙት ህይወት አማካኝነት ሙሉ በሙሉ ተቀባይነትን ያገኙ ቢሆንም እንኳ በራሳቸው መንገድ መቀበልንም ሆነ ተቀባይነትን ለማገኘት የሚጥሩና የሚጋደሉ ናቸው (ኤፌ 1፡6) ፡፡ ሁሉም አማኝ በእግዚአብሔር "ተቀባይነትን ማግኘት"(4) ችሏል ብዙዎች ግን ጽድቃቸውንም ሆነ ተቀባይነት ማግኘታቸውን በእምነት መቀበል አቅቷቸዋል(2 ቆሮ 5፡21) ፡፡

እንዲሁም ደግሞ "በሙላት መሰጠት" (5) ህይወታቸውን ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በጠቅላላ የተማረከ የሚያደርጉ ጥቂቶች ናቸው፡፡ ይህ እርሱ የፈለገውን ሁሉ በእኛ፣ ከእኛ ጋር፣ ለእኛ ወይም በእኛ በኩል ያደርግ ዘንድ ለእግዚአብሔር ፈቃዳችንን በማይቀለበስ ውሳኔ የመስጠት እርምጃ ነው ።ይህን ስናደርግ መብታችንን ሁሉ እንተዋለን።

እንዲህ አይነቱን ውሳኔ ከወሰንን በኋላ ብዙ ጊዜ ሁኔታዎች ወደ ቀውስነት እስኪደርሱ ድረስ ይበለሻሻሉ። ምክንያቱም ህይወታችንን ሙሉ በሙሉ እንዲቆጣጠር መጠየቃችንን እግዚአብሔር ስለሚያከብር ነው። እርሱ የመቆጣጠሩን ድርሻ የወሰደ ከሆነ የእኛ ድርሻ ሊቆም ይገባል ያ ደግሞ ብዙም ደስ የሚያሰኝን አይሆንም ። ህይወታችንን መቆጣጠራችን ወደፍጻሚ እንዲመጣ እግዚአብሔር የሚጠቀምባቸው ሁኔታዎች ወይም ሰዎች ብዙውን ግዜ በራሳቸው መንፈሳዊ ያልሆኑ ይሆናሉ። እናም አንዳነዴ ያልተገባ መከራን ያመጡብናል። እንዲህ ያሉ መከራዎች ናቸው የእግዚአብሔርን እቅድ በህይወታችን ውስጥ የሚያሳኩት (1 ጴጥ 2፡20-21፣ ፊሊ 1፡23-30)። በመከራ ወይም በቅጣት ወቅት ( ፊሊ 3፡10፣ ዕብ 12፡11) አልፎ አልፎ ሁኔታው ደስ ለመሰኘት ምክንያት የሚሆን ይመሰለናል ነገር ግን እርሱ የምንናፍቀውን  ቅድስና ለማምጣት የሚሆን የምንሰራበት መቀረጫችን ነው።።

እግዚአብሔር ለአማኞች ያለው አላማ የክርስቶስን መልክ እንዲመስሉ ነው (ሮሜ 8፡29)። እርሱን የመምሰል ሂደት በመከራ ማለፍንም ያካትታል።  በሮሜ 8፡28 "ነገር ሁሉ" በመባል ለበጎ እነደ ሚደረጉ የተጠቀሱት ሁሉ በራሳቸው በጎ እንደሆኑ አልፎ አልፎ ነው የታየው።

## የውስጥ ግጭቶችህ

ከላይ ባለው የክብ ሥዕል ውስጥ “S” የሚወክለው በራስ-ገዝ የሚመራን ህይወት ወይም “ስጋን” ነው (ኪንግ ጀምስ ትርጉም)። ስጋ በብዙ አማኞች ህይወት ውስጥ ለመላው የክርስቲያናዊ ልምምዳቸው የበላይ ገዢ ነው። በአሉታዊም ሆነ በአዎንታዊ መንገድ የሚፈልገውን ነገር በአንዳች ነገር ወይም ሰው እንዲሟላለት በግለሰቡ ላይ ጥገኛ ሆኖ የተለያዩ ነገሮችን ይሻል። ገንዘብ፣ ቁሳዊ ነገሮች፣ ስኬት፣ ዝና፣ ወሲብ፣ ሥልጣን ወይም የትኛውም አይነት የማይቆጠሩ የሆኑ ሊሎች ነገሮች ሰውን ያነሳሱት ወይም ይነዱት እና በገዛ ራሱ ህይወት ወይም ስጋ የሚገዛ በሚሆንበት ጊዜ ማእከላዊ ትኩረቱ ራሱ ይሆናሉ። ከዚያ አማኝ የክርስትና ህይወት በገዛ ራሱ ብርታት ለመኖር የሚጥረው የስጋ ጥረት ይሆንበታል።

በህይወታችን ያለውን የክርስቶስን ማእከላዊነት በሌላ በማንኛውም ነገር ስንተካ ሌላው ቢቀር እኛ ራሳችን በህይወታችን ዙፋን ላይ ማንኛውንም አይነት ነገር ለማስቀመጥ ብንፈቅድ ያ ጣኦት ይሆናል። ከዚህ የተነሳ ለክርስቲያን “ስጋ” ጣኦትን የማምለክ ያክል የከፋ ችግር ይሆንበታል። ስለዚህም እግዚአብሔር በስጋ ላይ አጥብቆ ይነሳል። እርሱ ብዙ ጊዜ በራስ የሚመራ ህይወትን ብቃት አልባነት ለመግለጥ አማኙ ያለበት ሁኔታ ሊሸከመው የማይችለው ሆኖ እስኪያገኘው፣ በራሱ ተስፋ እስኪቆርጥና በገዛ ራስ-መር የሚመራውን ሕይወት አመራር በክርስቶስ ህይወት ለመለወጥ እስኪፈቅድ ድረስ እግዚአብሔር በስጋ ላይ ይነስል።

የገዛ ማንነት (ስጋ) የሚቆጣጠር ሆኖ እስካለ ድረስ በ “ነፍስ” (ስብዕና) ውስጥ ያሉት በ ክቡ ሥዕል ውስጥ የተጠቀሱት ግጭቶቸ የሚቀጥሉ ይሆናሉ። እድሜና ሀላፊነቶች እየጨመሩ በሄዱ መጠን ግጭቶቹ እየባሱ ሊሄዱ ይችላሉ። አልፎ አልፎ በስነልቦናዊው ሁኔታ በጥሩ የተደላደለ በራስ የሚመራ ህይወት በብዙ የህይወት ቆይታው የሚያጋጥሙትን ሁኔታዎች ሊወጣቸው ይችላል። ነገር ግን ውጤቱ ከተፈጻሚነት እጅግ የራቀ ነው።

የስነ ልቦና ጉድለቶች (እውነተኛም ሆነ ምናባዊ የሆኑት) የበደለኛነት ስሜቶች ጋር የተለያዩ አይነት ተስፋ መቁረጦችን ለማምጣት በራስ-ገዝ ህይወት ላይ ይጣመራሉ። እንዲህ አይነቶቹ ተስፋ መቁረጦች መፍትሄ ሊኖራቸው ይገባል። አንዳንዶች እነኝህን ስሜቶች በሌሎች ላይ በአካላዊ ጥቃት ወይም በቃላት አማካኝነት ለማራገፍ የሚመርጡ ሲሆኑ ሌሎች ደግሞ አጸፋውን በመፍራት ጥላቻቸውን የቻሉትን ያክል አምቀው ያቆያሉ። ሌሎች ደግሞ ቁጣቸውንና ተስፋ መቁረጣቸውን አምቀው ይይዛሉ። ይህም የሚሆንበት ምክንያት ለየትኛውም ችግርና ለሚያጋጥሟቸው እውከቶች ሁሉ ራሳቸውን ተጠያቂ አድርገው ስለሚቆጥሩ ነው። ጥላቻና ተስፋ መቁረጦች በየትኛውም አይነት ምክንያት ሲታመቁ በአእምሮ ወይም ስሜት አልያም በሁለቱም ላይ ተጽዕኖ የሚፈጥሩ ናቸው። በውስጥ ያለ ጥላቻ ወይም ቁጣ ብዙውን ጊዜ መጫጫንን (ድብርትን) ወይም በስሜት ላይ ስጋትን ያስከትላል። አንዳንዶች አእምሯቸውን የተለያየ አይነት ማዘባቶች ወይም የእውነታ ክህደቶችን ለማድረግ ይጠቀሙበታል። ይህ ደግሞ እውነተኛ ችግር ከሆነው የራስ-ገዝ ህይወት ጋር የመጋፈጥን ሃላፊነትን እንዲሸሹት ያስችላቸዋል።

ስነ ልቦናዊ ግጭቶች ያለ መፍትሄ ሲራዘሙ ብዙ ጊዜ በሥዕሉ ለይ እንደተመለከተው አካላዊ ማጉረምረም ያስከትላሉ። አካላዊ ህመሞች ምንም እንኳ እውነት ቢሆኑም በራስ-መር ህይወት ውስጥ ጠልቆ ላለው ችግር ጠቋሚ ምልክቶችም ናቸው። ስለዚህ ስነ ልቦናዊ ችግሮች የነፍስ ችግሮችም ይሆናሉ።

## ነጻ መውጫህ

የራስ-መር ህይወትን እግዚአብሔር በሚገዛና በሚያስተዳድርበት ጊዜ ሰው እነኝህ የስነልቦናና የስነ አካል የቀውስ ምልክቶች እንዴት መጥፋት እንደሚጀምሩ ያስተውላል።

የቀጥተኛው መስመር ሥዕል የሚያሳየው “ከሞት ውጭ የሆነውን ህይወት” መርህ ነው። ያም ደግሞ እግዚአብሔር የውስጥ ግጭትን የሚፈታበት መንገዱ ነው። አግድሞሹ መስመር የሚወክለው ዘላለማዊ የሆነውን የክርስቶስን ህይወት ነው። በትርጉም ደረጃ ዘላለማዊ ስንል የሚጠቁመው ምንም ጅማሬም ሆነ ፍጻሚ የሌለው መሆኑን ነው። ዘላለማዊነት በየትኛውም አቅጣጫ የጊዜ ገደብን አልፎ የሚሄድ ነው። ክርስቶስ እግዚአብሔር በመሆኑ እርሱ ሁል ጊዜ ኖርዋል ደግሞም ሁል ጊዜም ይኖራል። የእርሱ ህይወት ትናንትናም፣ ዛሬም እስከ ለዘለአለምም ያው ነው (ዕብ 13፡8) ። በመስመሩ የግራ ክንፍ ላይ እንደተመለከተው ክርስቶስ ሰው “ስጋ” ሆነ (ዮሐ 1፡14) እናም ለ 33 አመታት ያክል በሰው ሰውነት ኖረ። ከዚያም ተሰቀለ፣ ሞተም ተቀበረ እና በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተነሳ (1 ቆሮ 15፡3-4)። እርሱ ዛሬም ህያው ሆኖ ይኖራል (ዕብ 7፡25)። የዘላለም ህይወት ለአማኝ የአሁኑና የሚመጣው ጊዜ እውነታ ብቻ ሳይሆን ነገር ግን የዘላለም ሙላትንም ያካተተ ነው።




**የቀጥታው መስመር ሥዕላዊ ማስረጃ**

(ለበለጠ መረጃ ደስታ በሚል የተዘጋጀውን ክፍል **2** ተመልከት)

ዳግም እስካልተወለድን ድረስ (ዮሐ 3፡3) በክርስቶስ ዘላለማዊ ህይወት ውስጥ አይደለንም። ይልቁንም በመንፈስ ሙት በሆነው አዳማዊ ህይወት ውስጥ እንጂ። አንድ ሰው ያንን ማየት የሚችለው በሥዕሉ ላይ ካሉት የቀደሙ አባቶቻችንን ከሚወክሉት የተቀራረጡ የሰያፍ መስመሮች ጠፍተው ቢሆን ኖሮ እኛን አይመለከተንም ነበር በቀጥታ ለመናገር ሕይወታችን በአዳም ጅማሬ ያለው ነው። ስለዚህ በእርሱ ላይ የሆነው ነገር ሁሉ በእኛም ላይ ይሆናል። እርሱ ሀጢያት ሲሰራ እኛም ሰርተናል። እርሱ በሀጢያት ምክንያት ሲሞት እኛም አብረን በንፈሳዊው ሞት ሞተናል። ልክ አያቶቻችን ልጅ ሳይወልዱ ሞተው ቢሆን ኖሮ እኛም ሞተን እንደምንቀር ማለት ነው። እኛ ሁላችን በመንፈሳችን ሙታን ሆነን የተወለድን ስለሆነ በመንፈሳችን ከእግዚአብሔር ተለይተናል። ስለዚህ ለሀጢያታችን ይቅርታና ለመንፈሳችን ህይወትም ያስፈልገናል። ጌታ እየሱስ ክርስቶስ የመጣው ለሀጢያታችን በመሞት ምህረትን እናም የእርሱን የትንሳኤ ህይወት ለእኛ በመስጠት በሁለቱም አቅጣጫ ሙላትን ሊሰጠን ነው(ዮሐ 10፡10)።

ምናልባትም አንተ አማኝ ከሆንክ ይህንን ጠንቅቀህ ታውቅ ይሆናል ላታውቀው የምትችለው ግን የሚከተለውን ነው። አካላዊው ሞት ለአማኝ በአለም ካለ ሀጢያትና ህይወት መውጫና ወደ እግዚአብሔር ህልውና መግቢያ መንገድ ነው። እንዲሁም በተመሳሳይ ሰው ዳግም ሲወለድ ለስጋ በመሞት ሀጢያተኛ ከሆነው የአዳም ህወት ይወጣና በዳግም ልደት ወደ ዘላለማዊው የክርስቶስ ህይወት መግባት ይችላል። በዳግም ልደት ሰው ለአዳማዊው ህይወት ሞቶ ነጻ በመውጣት በክርስቶስ ህይወት ተወልዶ ህያው ይሆናል።

ሁለት ተቃራኒ የሆኑትን የአዳምንና የክርስቶስን ህይወት በአንድ ጊዜ ልንይዝ አንችልም። በእርሱ ስናምንና ዳግም ስንወለድ ክርስቶስ ወደ ህይወታችን ይመጣል አዲስን ህይወት ይሰጠናል ነገሩ በዚህ ብቻ አያበቃም እኛም የእርሱን ህይወት አንድ ለአንድ ተካፋዮች እንሆናለን። ሮሜ 6፡3 ወደኢየሱስ ክርስቶስ (ወደ እርሱ ህይወት) ብቻ ሳይሆን በሞቱም ጭምር እንደተጠመቅን ይናገራል።

***ማንነትህ***

ክርስቶስን በእምነት ስንቀበል በመስቀል ላይ ሰለሀጢያት በሞት የከፈለውን ዋጋ የራሳችን እናደርጋለን ከዚያም በላይ ዘላለማዊ ወደ ሆነው የክርስቶስ ህይወት ውስጥ እንገባለንም ያ ማለት የህይወታችንን ጅማሪውንም ሆነ ፍጻሚውን የሚጠቀልል ይሆናል። በሌላ አባባል ለማስቀመጥ ከአዳም ዘር የተያያዘውን መጥፎውን የህይወት ሰንሰለታችንን በጥሰን መልካምና ዘላለማዊ በሆነው የክርስቶስ ህይወት እንለውጣለን። በዚህም አዲሱን የህይወት ዘር እንቀዳጃለን የክርስቶስንም ህይወት እንወርሳለን። በሞቱ፣ በቀብሩ፣ በትንሳኤው፣

በእርገቱና በሰማያዊው ስፍራ መቀመጡንም እንካፈላለን (ሮሜ 6፡3-6፣ ገላ 2፡20፣ ኤፌ 2፡6)። እርሱ አንድ ብቻ ህይወት አለው ያም ደግሞ በአዲሱ ልደታችን ወቅት የምንቀበለው ህይወት ነው (1 ዮሐ 5፡11-12)

ከክርስቶስ ጋር እንደተሰቀለን በግል የእምነት ልምምድ እስካላወቅን እና እስክናውቅ ድረስ በአሮጌው የራስ-መር ህይወታችን በተማርናቸው መንገዶች ለክርስቶስ ለመኖር መሞከራችንን እንቀጥላለን። ከአዳም በነበረን የሽንፈት ታሪክ መሰረት በውስጣችን ያሉ ግጭቶች መጫንና ማሸነፋቸውን ይቀጥላሉ። ነገር ግን በክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ በእምነት ሆነን ትክክለኛ የሆነውን ቦታችንን በመስቀል ላይ ስንይዝ ያኔና ያኔ ብቻ ነው እኛ በእውነት "በህይወት አዲስነት መመላለስ" የምንችለው (ሮሜ 6፡4) ።ያም አሮጌው ነገር የሚያልፍበትና እነሆ ሁሉም አዲስ የሚሆንበት ይሆናል (2ቆሮ 5፡17)።

ወደ መስቀሉ የምናደርገው ጉዞም ሆነ መስቀሉ በራሱ የመከራ ጉዞ ነው። ይሁን እንጂ የመከራውን ጉዞ ማብቂያው ብቸኛ መንገድ ያ የመስቀሉ ጉዞ ብቻ ነው። በመስቀሉ ያገኘነው ልምምድ (ከክርስቶስ ጋር በሞተና በትንሳኤው መካፈላችን) በመንፈስ ለተገዛ ህይወት ለመኖር ያስቻላንን በር ያገኘንበት መንገዳችን ነው (ገላ 5፡16)። ይህ ህይወት በሞት አልፎ የተገኘ ህይወት፣በመሸነፍ አልፎ የተገኘ ድል ደግሞም በአማኝ ህይወት ለሚያልፍ የትኛውም መከራ አላማውን ማስረጃ ነው፡፡

የውስጣዊ ግጭቶችህን እና የማያቋርጥ ሽንፈቶችህን በእምነት አስወግደህ ለመኖር እስክትዝል ድረስ መታገል ሰልችቶሀልን? የአንተ ለሆነው ነገር ሁሉ ሞተህ የእርሱ ለሆነው ነገር ሁሉ ለመኖር ፈቃደኛ ነህን? ይህ እንዲሆንልህ የራስ-መር ህይወትህን በክርስቶስ-መር ህይወት መለወጥና በመንፈስ ቅዱስ መሞላት እንዲሁም በቁጥጥሩ ስር መሆን ያስፈልግሀል። ይህን እንቢ ማለት በግጭት፣ መከራ እና ሽንፈት ውስጥ ለሚኖር ስጋዊ ህይወት በመገዛት የእግዚአብሔርን መንፈስ በማሳዘን ለመኖር መወሰን ነው።

### የደንነት ጸሎት

ነገሮችን በራስህ መንገድ በማድረግ የሚከሰቱ ግጭቶች አሰልችተውህ ከሆነ በእምነት ራስህን ለክርስቶስ ስጠው እርሱ ነጻ ያወጣህና የራሱን ፈቃድ በአንተ ይፈጽማል። ክርስቶስን የግል አዳኝህ አድርገህ አልተቀበልክ እንደሆነ መጀመሪያ ማድረግ የሚያስፈልግህ በመንፈስ ዳግም ልደትን እና አዲስን ህይወት እንዲሰጥት ለእግዚአብሔር ፈቃደኛነትህን መግለጽ ነው። በፈቃደኛነት እና በታማኝነት ይህን ጸሎት ብትጸልይ ዳግመኛ ልትወለድ ትችላለህ።

"በሰማይ ያለህ አባት ሆይ እስካሁን ድረስ በአዳም ህይወት ያለሁ ሐጢአተኛ መሆኔን ተረድቻለሁ ደግሞም ሐጢአትን ሰርቻለሁ። ብቸኛውን ልጅህን ጌታ እየሱስ ክርስቶስን በእኔ ፋታ ስለሀጢያቴ እንዲሞትልኝ እንደላከውም አምናለሁ። እርሱ እነደሞተልኝ፣ ከሙትም እንደተነሳና አሁንም ህያው ሆኖ እንደሚኖር አምናሉ። በዚህ ቅጽበት አዳኜ አድርጌ እርሱን በመንፈሴ እቀበለዋለሁ። እኔነቴን፣ ያለኝን ሁሉ እና ለአንተ ልሆን የሚገባኝን ሁሉ ለእርሱ አስገዛለሁ። ከሐጢያቴና ከራስ ወዳድነት ህይወቴ ስላዳንከኝና በክርስቶስ ባገኘሁት አዲስ ህይወት እንድኖር ስለረዳኸን አመሰግንሃለሁ። "አሜን"

### የመለያ ጸሎት

"የደንነት ጸሎት" ከጸለይክ ዳግመኛ ተወልደሃል፣እግዚአብሔር በክርስቶስ ለሚያምኑ ሁሉ የእርሱ ልጆች እንዲሆኑ እድል እሰጣለሁ ብሏል (ዮሐ 1፡12)። እንግዲህ ቀደም ሲልም ሆነ አሁን ለደንነት ጸልይክ ከሆነ "የመለያ ጸሎቱን" መጸለይህ የክርስቶስን የድል ህይወት እና ሰላም እንድትለማመድ ያደርግሀል። ይህን ጸሎት ከመጸለይህ በፊት የራስ-መር ህይወትህ በእርግጥ የሰለቸህ ልትገላገለው የምትፈልግነልትሆን ይገባል። የክርስትናን ህይወት በራስህ ጥረት ለመኖር በመሞከርህ በመንፈስ ቅዱስ የምትወቀስ እናም ህይወትህን መቆጣጠርህን ለመተው ዝግጁ የሆንክ መሆን ይኖርብሀል። ይህ ሁሉ በእውነት የሚሰማህ ከሆነ እንዲህ ልትጸልይ ትችላለህ።

"አባት ሆይ ሐጢአቴን ይቅር ስላልክ እና ከአዳም ህይወት ስላላቀከኝ እንዲሁም ወደክርስቶስ ህይወት ስላመጣኸኝ አመሰግንሀለሁ። አሁን እኔ በክርስቶስ ነኝ፣ ከእርሱ ጋር እንደተሰቀልኩ፣ ከእርሱ ጋር እንደተቀበርኩ፣ ከእርሱ ጋር እንደተነሳሁ እና በአንተ ቀኝ ከእርሱ ጋር እንደተቀመጥኩ አምናለሁ። ከዚህች ቅስበት ጀምሮ የአንተን ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስን እመርጣለሁ፣ በርሱን ህይወት እኔ እኖራለሁ። እራሴን ለሐጢአት እንደሞትኩና ለአንተ እንደምኖር አድርጌ እቆጥራለሁ። ከክርስቶስ ጋር መሞቴን ስረሳና የእርሱን ህይወት በራሴ ሰብዐዊ ጥበብ ለመኖር ስሞክር መንፈስ ቅዱስ እንዲያነቃኝ እፈቅዳለሁ። ለጽድቅ እንጂ ለሀጢያት ጥቅም እንዳይውል እንደ ጽድቅ መሳሪያ አድርጌ ሁለእንተናዬን በፈቃዴ ለአንተ እሰጣለሁ። ክርስቶስንና የእርሱን ህይወት ለእኔ እውን ስላደረግህ አመሰግናለሁ። ራስህን በእኔ አክብረው። በኢየሱስ ስም እጸልያለሁ። አሜን"